# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 1-28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከማርች 1-31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2022
አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ... 3
ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... 4
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ... 5
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ... 6
ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ... 6
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ... 7
ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... 7
ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 7
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ. 8
ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 8
እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ... 9
ጠባይ አዝማሚያ ... 9
እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 9
እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 10


## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር አብዛኛዉን ጊዜ ሞቃታማ እና ፀሃያማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ የቆየ ቢሆንም፤ በሶስተኛዉ አስር ቀናት ላይ በደቡብ ምዕራባዊ ህንድ ዉቂያኖስ ላይ በተደጋጋሚ ተፈጥሮ የነበሩት የባህር ላይ ሞገዶች (Tropical Cyclones) በመዳከማቸዉ እና እርጥበት አዘል አየር ወደ ሀገራችን መግባት በመጀመሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እንዲኖር አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በመካከለኛዉና ምስራቅ አማራ እንዲሁም በጥቂት የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በመካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በቄለም ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በኢሉአባቦርና ጅማ፣ በምዕራብ አርሲና ጥቂት ምዕራብ ጉጂ፣ በሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች እና በሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከ5-81 ሚሜ የሚደርስ ከ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሰሜን፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ በአዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሆሮ ጉዱሩ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በበጥቂት የምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ በኢሉባቦርና ጅማ፣ በሸካ፣ በከፋና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች ዝናብ ነበራቸዉ፡፡


ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7   ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8   ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በአጠቃላይ በፌብሪዋሪ ወር የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በመጀመሪያዎቹ እና በሁለተኛዎቹ አስር ቀናት ሞቃታማ እና ፀሃያማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ የቆየ ሲሆን፤ ነገር ግን በሶስተኛዉ አስር ቀናት በተለይም አስቀድመው ተፈጥረው የነበሩ የባህር ላይ ሞገዶች እየተዳከሙ በመሄዳቸው ምክንያት የተወሰነ እርጥበት ወደ ሀገራችን እንዲገባ ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተወሰነ እርጥበት አግኝተዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በመካከለኛዉና ምስራቅ አማራ እንዲሁም በጥቂት የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደመዘገቡ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች አመልክተዋል። በወሩ የተገኘው እርጥበት የበልግ ሰብል በስፋት አምራች ለሆኑት ለደቡብ ምእራብ አካባቢዎችም ሆነ ለሰሜን ምስራቅ እና ለመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከነበረው አስተዋፅዎ ጎን ለጎን ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በመጠኑም ቢሆን በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከፊብርዋሪ 1-28/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ በሀገሪቱ የደቡብ ምዕራብ የሚገኙ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ስር እንደነበሩ ተስተውሏል፡፡ በዚህም መሰረት በጥቂት መካከለኛው ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ ይጠቀሳሉ፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገርቱ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 10) (ካርታ 10) ፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከቀደመው ወር በተሻለ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ሲሆን፤ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል።

በሚቀጥለው የማርች ወር ለዝናብ መፈጠር መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ ወደ ሀገሪቱ ሊገባ በሚችለው እርጥበታማ የአየር መጠን መቀነስ ጋር ተያይዞ በወሩ ውስጥ ደረቃማ ቀናት ሊዘወተሩ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

<u>በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የአርሲና የባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር፣ የባህዳር ዙሪያ፤ ጋምቤላ፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛ፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ደግሞ ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

# እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር እያሳየ የሚሄድበትና የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠናከርበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለበልግ እርሻ ሥራ የማሳና የዘር ዝግጅት የሚካሄድበት ወቅት ነው፡፡

የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ መረጃ እንደሚያሳየው በሚቀጥለው የማርች ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን በአንጻራዊ ሁኔታ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የሀገሪቱ ክፍልች በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችል ይጠባቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ አብቃይ አካባቢዎች ለበልግ እርሻ ሥራዎች፣ ለአፈር እርጥበት መጠናከር፣ ለማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን በወሩ ውስጥ ወደ ሀገሪቱ ሊገባ የሚችለው እርጥበታማ አየር መጠን በየጣልቃው እንደሚቀንስ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ደረቃማ ቀናትም ሊዘወተሩ ይችላሉ ይህም ሁኔታ በበልግ እርሻ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በመሆኑም የበልግ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የሚከሰተውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚመለከታቸው ክፍሎች የተገኘውን እርጥበት በአግባቡ በመያዝና በመጠቀም ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው በማርች ወር በአብዛኛዎቹ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት መጠን ከቀን ወደ ቀን በአንጻራዊ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የሀገሪቱ ተፈሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የተራዘመ ደረቅ ሰሞን በመኖሩ ከሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ ደረቅ ሁኔታም እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ በዚህ ወቅት የቀኑ ሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ በውሃ አካላት ላይ ከፍተኛ የትንነት መጠን የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ የውሃ አጠቃቀማችን ለብክነት የሚያጋልጥ እንዲሆን እንጠቁማለን፡፡